# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

***ታህሣሥ 30 ቀን 2003 ዓ.ም.***

**-በወያኔ ካድሬዎች መሀከል አዲስ የእርስ በርስ ሽኩቻ ተጀመረ፤**

**-ብዙ ባለስልጣናት ከአዲስ አበባ መስተዳድር ተነሱ፤ ተባረሩ፤**

**-የኑሮ ውድነቱ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደረሰ፤**

**-መለስና ነጋዴው ህብረተሰብ ለአንድ ቀን ሲነታረኩ ዋሉ፤**

የወያኔ ባለስልጣናት በጥቅም ግጭት የተነሳ እርስ በርስ ከመሻኮታቸውም በተጨማሪ አንዱ አንዱን ጠልፎ ለመጣል በግምገማ ሰበብ እየተራወጡ መሆኑ ተጋለጠ።

መለስ ዜናዊ በአምስት አመት ግዜ ውስጥ ይተገበራል ብሎ በአንድ ሌሊት ሞነጫጭሮ ያቀረበውን እቅድ ህግ አድርገው አጸድቀው ተግባራዊ ለማድረግ እየተፍጨረጨሩ ባለበት ሰዓት እርስ በርስ በጥቅም እየተጋጩ መፍረክረክ መጀመራቸው ታውቆዋል።

አቅብጦና አወላግዶ ያስቀመጣቸው ባለስልጣናት በህዝብ ሀብት እንደልባቸው ሲጫወቱ ኖረው አንዳችም እርምጃ ሳይወስድባቸው ዛሬ ለይመሰል ሙስና ፈጽማችሁዋል እያለ ቢለፍፉም አድማጭ አጥቶ እኛም የድርሻችንን ነው የወሰድነው በሚል ምላሽ እየሰጡ ከፍተኛ እና መሀከለኛ የተባሉት ካድሬዎች እርስ በርስ እየተወዛገቡ መሆኑ ታውቆዋል።

ኪራይ ሰብሳቢነት በከፍተኛ ሁኔታ በካድሬዎቻችን ውስጥ ተንሰራፍቶ የጀመርነውን የትራንስፎርሜሽን እቅድ እያደናቀፈ ይገኛል ያለው የወያኔ ግምገማ ሁሉም ባለስልጣናት

በሙስና የነቀዙና የተጨማለቁ በመሆናቸው የትኛውን ከየትኛው መለየት ተቸግረው ለሰባት ቀናት ውለው ቢያመሹበትም አንዳችም ለውጥ ሳያሳዩ መለያየታቸው ታውቆዋል::

የኦህዴድን ካድሬዎች በሶስት ቦታ በመከፋፈል ወጥሮ ይዞዋቸው የከረመው ወያኔ የብአዴንን በባህርዳር የደኢዴንን ካድሬዎች በአዋሳ የስንግ በመያዝ አላላወስ ቢላቸውም ካድሬዎቹ ግን ከፍተኛ ባለስልጣናት የሚሰሩትን እና እየሰሩ ያሉትን ምዝበራ ስለሚያውቁ ያለ አንዳች ይሉኝታ እና ሀፍረት እኛ ም የድርሻችን ነው በማለት ምላሽ በመስጠታቸው እነ መለስ ግራ እንደተጋቡም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

በአዳማ ፣በጅማ እና በነቀምት መሀከለኛ የተባሉትን የኦህዴድ አመራሮችና ካድሬዎች የክልሉ ፕሬዝዳንት እና የኦህዴድ ሊቀመንበር አለማየሁ አቶምሳ እና የኦህዴድ ምክትል ሊቀመንበር የመለስ አማካሪ ሆኖ የተሾመው ሙክታር ከድር በግምገማ ወጥረው ለ7 ቀናት ያቆዩዋቸው ቢሆንም አንድም የረባ ነገር ሳያገኙበት በማስፈራራት እና በማስጠንቀቅ ብቻ እንዳሰናበቱዋቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

ደኢህዴን የተባለው የወያኔ ጨቅላ ተለጣፊም ቢሆን በአዋሳ ባደረገው ግምገማ መሀከለኛ የተባሉት የወረዳ እና የዞን አስተዳደር ባለስልጣናቶችን ቢያስፈራራም ጠብ ያለለት ነገር ባለማግኘቱ በማስጠንቀቂያ እና ለይምሰል በማስፈራራት የበተናቸው ቢሆንም ይልቁንም ባለስልጣናቱ ከወትሮው በበለጠ የልብ ልብ ተሰምቶዋቸው በህዝብ ላይ መቀለድ እንደጀመሩ ለማወቅ ተችሎዋል::

ብአዴንም በበኩሉ በባህርዳር ባደረገው ግምገማ ላይ የሰላ ትችት ያቀረበ ቢሆንም ሙስና ተንሰራፍቶዋል ማጥራት ይጀመር ከተባለ መጀመሪያ መጀመር ካለበት ከቁንጮው ከመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍንና ከከፍተኛ ባለስልጣናት ነው እንጂ ከእኛ መሆን የለበትም በሚል መከራከሪያ ሀሳብ አምጥተው ሲታመሱ የሰነበቱ ሲሆን እነሱም እንደ ሌሎቹ የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች ሁሉ በማስፈራሪያና በማስጠንቀቂያ ብቻ እንደታለፉ ታውቆዋል::

የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ለ20 ዓመታት የሀገር እና የህዝብ ሀብት በሚስት ፣በልጆቻቸው እና በዘመዶቻቸው ስም ግጠው እና ጠርገው አግበስብሰው ከጨረሱ በሁዋላ ዛሬ የሀገሪቱ ካዝና ባዶ መሆኑን ሲያረጋግጡ በወረዳ እና በዞን ብሎም በቀበሌ ሹማምንቶች ላይ ወንጀሉን ለመደፍደፍ እና ተጠያቂ ሊያደርጉዋቸው ቢሞክሩም ሳይሳካላቸው እንደቀረም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

በመለስ አይዞዋችሁ ባይነት ከሀገር እና ከህዝብ ላይ ሲመዘብሩ የኖሩት እነኚሁ ባለስልጣናት በገንዘብ ልባቸው ተደፍኖ ባለበት በአሁኑ ወቅት እነ መለስ አጣብቂኝ ውስጥ ሲወድቁና ግራ ሲገባቸው መልሰው ሊቆጡና ብሎም ሊቆነጥጡዋቸው ቢሞክሩም ተመልሶ ጥያቄው ወደ ራሳቸው በመዞሩ ለይምሰል በማስጠንቀቂያ ብቻ ለማለፍ እንደተገደዱ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከህዝብ እና ከሀገር ሀብት ላይ ዘርፈው ዛሬ አንቱ የተባሉ ቱጃሮች የሆኑት የወያኔ ባለስልጣናት ከጥቂት ደጋፊ ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር ገበያውን ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠሩት ከመሆኑም በተጨማሪ እነሱ እንዳሻቸው እያመሱት ባለበት ወቅት መለስ ዜናዊ ጭምር መቆጣጠር አቅቶት እንደገና በመለማመጥ ላይ እንደሚገኝ ታውቆዋል::

ህዝቡ የኑሮ ውድነት የስንግ ወጥሮ ይዞት አላላውስ ብሎ በተቸገረበት በዚህ ወቅት ገበያውን የበለጠ እንዲከርር እና እንዲጦዝ እነዚሁ የወያኔ ረጅም እጅ ያላቸው ባለስልጣናት ከጥቂት ነጋዴዎች ጋር በመመሳጠር ንግዱን እያመሱት ከመሆኑም በላይ በአንድ ጀምበር ብቻ የዕቃዎች ዋጋ ተቆልለው እንዲንር እያደረጉ በህዝቡ ስቃይ እየተዝናኑ እና ተጨማሪ ሀብት እያግበሰበሱም እንደሚገኙ ታውቆዋል፡፡

መለስ በአንድ ሌሊት  ዕፎ ያቀረበውን እና ህግ ሆኖ የጸደቀውን የአምስት ዓመቱን የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በአፋጣኝ ተግባራዊ ይደረግ በማለት ቢወተውትም በሙስና እስከ አንገታቸው የተዘፈቁት ከፍተኛም ሆነ መሀከለኛ የተባሉት ባለስልጣናት የዘረፉት የህዝብ ሀብት አላላውስ ብሎዋቸው እያደናቀፈ እየጣላቸው መንቀሳቀስ ባለመቻላቸው የመለስ እቅድ ከወዲሁ ገደል እየገባ እንደሚገኝ እየታየ ይገኛል ተብሎዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ውስጥም የሚገኙ መሀከለኛ ካድሬዎች እንደ ሌሎቹ ክልሎች ሁሉ ግምገማ ማድረግ የጀመሩ ከመሆኑም በላይ እርስ በርስ እየተሞላለጩ ከፍ ዝቅ እየተባባሉ ከ10 ቀናት በላይ መፍጀታቸው ታውቆዋል፡፡

በህላዊ ዮሴፍ ምትክ የአዲስ አበባ የወያኔ ተጠሪ ሆኖ ተሹሞ የነበረውን የደቡብ ሰው ሬድዋን ሁሴን የተባለውን ተክቶ በቅርቡ ተሹሞ ስራ የጀመረው ልዑልሰገድ ይፍሩ በተባለው የብአዴን ካድሬ የሚመራው ይሄው የአዲስ አበባ ባለስልጣናት ግምገማ እርስ በርስ ከመወራረፋቸው በተጨማሪ የተደበቁ ምስጢሮችን እያጋለጡ የወያኔን ገመና እያዝረከረኩ እንደሰነበቱም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ግምገማውን እንዲመራ የተላከው ይሄው አዲስ ሹመኛው የወያኔ በረሀ አመጣሽ ካድሬ በተለይ በነባር  በረሀ አመጣሾች እና በቅርቡ የመለስን ድርስት ተግባራዊ ያደርጋሉ ተብሎ ተስፋ ተጥሎባቸው በተሾሙት አዳዲስ ካድሬዎች መሀከል መናናቅ  በመስፈኑ እጅግ ተራ በሆኑ ቃላት ጭምር ሲወራረፉና ሲሰዳደቡ እንደከረሙ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በዚህ ብቻ ሳያበቃ አዳዲሶቹ በሙሉ አቂዋም በመያዝ እስከዛሬ ከህዝብ ላይ ዘርፈው ሀብት ያከማቹ ባለስልጣናት በህግ እንዲጠየቁ ካልተደረገ እኛም የበኩላችንን ሊሰጠን ይገባል በማለት በድፍረት እስከ መጠየቅ  ደርሰው እንደነበረም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

በሁለቱ ካድሬ ቡድኖች መሀከል የተጀመረው ሽኩቻ ከቀን ቀደ ቀን እያደገና እየሰፋ በመምጣቱ የወያኔ ሹመኛው ልዑልሰገድ የተባለው ግለሰብ በየቀኑ የሚደርገውን ውይይት እና እንቅስቃሴ ማታ ማታ ለመለስ ይዞ እየቀረበ የሚነጋገሩበት ሲሆን በቅርቡም ብዙ የአዲስ አበባ ሹመኞች በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ሰጪነት በኩማ ደመቅሳ ፈራሚነት  እንዲታገዱ መደረጉም ታውቆዋል፡፡

ለመለስ ድርሰት እንቅፋት ናቸው ብሎ በስም ዝርዝር ያቀረበለትን አዳዲስ እና ነባር በረሀ አመጣሽ ካድሬዎችን ባለፈው ሳምንት ውስጥ ግምገማው ሳይጠናቀቅ ገና በሂደት ላይ በነበረበት ወቅት ለግዜው ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው ብቻ ተደርጎ ከስልጣናቸው እንዲነሱ መደረጉም ታውቆዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ካድሬዎች መሀከል ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ በመፈጠሩ ዝቅተኛ የተባሉት ካድሬዎች ብቻ በየወረዳው ስራ እንዲሰሩ ተደርጎ ከፍተኛ እና መሀከለኛ የተባሉት ግን በግምገማ ተወጥረው እንደሚገኙ ተጠቁሞዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የክፍለ ከተማ የስራ አስፈጻሚዎች እና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናትም በዚሁ እየተደረገ ባለው ግምገማ ተወጥረው የሰነበቱ ከመሆኑም በላይ ከሌሎቹ ክልሎች በተለየ ሁኔታ ጥብቅ እርምጃ እየተወሰደባቸው ሲሆን ከታህሳስ 11 ቀን ጀምሮ እስከ ታህሳስ 28 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ የመሰብሰቢያ አዳራሾች ውስጥ ተከታታይ የሆነ ግምገማ ከማድረጋቸውም በላይ አንዳንዶቹ በግምገማው እራሳቸውን እየሳቱ በተቀመጡበት እዚያው እየወደቁ መታየታቸውን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ እየተደረገ ባለው ግምገማ የየክፍለ ከተማ ስራ አስፈጻሚዎችን ጨምሮ ከፍተኛ አመራር የነበሩ 15 ያህል ነባር እና አዳዲስ ካድሬዎች ከስልጣናቸው የተነሱ ቢሆንም የመለስን ድርሰት ያፋልሳሉ በሚል ስጋት ሳይባረሩ ከደረጃ ዝቅ እየተደረጉ እንዲሰሩ ተብሎ መወሰኑን ዘግይቶ የደረሰን ጥቆማ አብራቶዋል::

ከቦሌ፤ ከአራዳ፤ ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ፤ከአቃቂ ቃሊቲ እና ከሌሎችም ክፍለ ከተሞች እየተመነጠሩ ያሉት የወያኔ ሹመኛ ካድሬዎች ከህዝብ እና ከሀገር ሀብት ላይ በዘረፉት ወንጀል በህግ መጠየቅ እና መታሰር ብሎም መባረር ሲገባቸው ተመልሶ ከደረጃ ዝቅ እየተደረጉ እንዲሰሩ መደረጉ የጀመሩትን ዘረፋ አጠናክራችሁ ቀጥሉ ተብለው የተመደቡ ያስመስላል ሲሉ ነዋሪዎቹ በቁጭት እና በንዴት ሲገልጹ ተደምጠዋል::

በ1993 ዓ.ም ወያኔ በተከፋፈለበት ወቅት ቁንጮው መሪ መለስ ዜናዊ «በስብሰናል .....ግን እንታደሳለን» በማለት በይፋ ስለ ስርዓቱ መቆሸሸና መብከት የተናገረ ሲሆን አሁን ደግሞ ከዚያን ግዜው በበለጠ ሁኔታ ከመቆሸሻቸውም በላይ በሀገር እና በህዝብ ሀብት የበሰበሱና የገደፉ መሆናቸውን እራሳቸው ካድሬዎቹ በይፋ እያረጋገጡ መሆኑ ታውቆዋል::

በሌላ ዜና የወያኔ ጥቅመኛ ካድሬዎች እና ስግብግብ ነጋዴዎች በመመሳጠር በህዝቡ ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት እንዲቆለል ከማድረጋቸውም በተጨማሪ የእቃዎች እጥረት እንዲፈጠር እና ምስቅልቅሉ እንዲወጣ እያደረጉም ይገኛሉ::

ወያኔ በሀገሪቱ ውስጥ በፈጠረው መሰሪ ተንኮል የተነሳ የኑሮ ውድነቱ ከቀን ወደ ቀን ከመቀነስ ይልቅ እያሻቀበ እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱም ተረጋግጦዋል::ከደደቢት በረሀ ጀምሮ ይዞት የመጣውን የመከፋፈል እና እርስ በርስ የማጋጨት ተንኮል አሁንም በነጋዴና በአምራቹ ...... በሸማቹና በነጋዴ መሀከል ክፍተት እንዲፈጠር እየሰራ መሆኑን የጠቆሙት የጉዳዩ ባለቤቶች ሰሞኑን ሲሰራ የነበረውም ይሄንኑ እንደነበር አጋልጠዋል::

ግራ የተጋባው የወያኔ ቡድን ለዘመናት ነጋዴውና አምራች ገበሬው ብሎም ሸማቹ በጋራ ተስማምተው ሲገበያዩና ሲለዋወጡ የኖሩ ቢሆንም ወያኔ ጭር ሲል አልወድም በሚል ብሂል እርስ በርስ እንዲከፋፈሉ እና የጎሪጥ እንዲተያዩ ከፍተኛ ሴራ ሲውጠነጥን የነበረ ቢሆንም እንዳሰበው እንዳልተሳካለት ለማወቅ ተችሎዋል::

ገበሬውን ሲያገኝ ተቆርቋሪ በመምሰል...... ነጋዴውን ሲያገኝ አትራፊ እንዲሆን ለማድረግ እየሰራ መሆኑን እየሰበከ...... ሸማቹን ደግሞ ዲሞክራሲ መብትህ ነው እያለ በተለያዩ ስልቶች ለመነጣጠል ሙከራ እያደረገ የሰነበተው የወያኔ አሸክላ ቡድን ያሰበው ሳይሳካ የዘረጋው ወጥመድ ሳይዝለት መና መቅረቱ ታውቆዋል።

በገበያው ውስጥ ዋጋ እንዲንር ሆን ብሎ እያሴረ የሚገኘው የወያኔ ቡድን የነዳጅ ዋጋ በዓለም ላይ እምብዛም ባልጨመረበት በአሁኑ ሰዓት በሀገር ውስጥ የአንድ ሊትር ቤንዚን 16 ብር እየተሸጠ ናፍጣ 14 ብር እየተገዛ በሀገር ውስጥ መጉዋጉዋዣ ንሮ የአውሮፕላን ትኬት መቁረጫ ሆኖ በተቆለለበት በአሁኑ ሰዓት ነጋዴውን ጥፋተኛ..... ገበሬውን ልግመኛ...... ሸማቹን የደላው እያለ እያሾፈና እየቀለደ እንደሚገኝ በተግባራዊ እንቅስቃሴው እየታየ መሆኑም ታውቆዋል።

በሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች በአግባቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህዝቡና ለተጠቃሚው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዳይደርሱ እራሱ ባደራጃቸው ቀድሞ ታጋዮች በነበሩ አዲስ ነጋዴዎች እጅ እንዲገባ አድርጎ በህዝቡ ላይ ጫና ከመፍጠሩም በተጨማሪ ህዝቡ በኑሮ ውድነት ላይ ብቻ ሌት ተቀን እንዲያስብ እያደረገ ይገኛል።

ዛሬ የአንድ ኪሎ ነጭ ሽንኩርት ዋጋ 40 ብር ገብቶ ፤ዘይት ከ27 ብር ወደ 40 ብር አሻቅቦ፤ጋዝ በየጊዜው በተደረገ ጭማሪ ህዝቡ ከመግዛት አቅሙ በላይ አናጥሮ የኑሮው ውድነት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ መልሶ ሸማቹን የደላው የሚል ቅፅል ስም ለጥፎለት እያሾፈ መገኘቱ አሳፋሪና አሳዛኝ መሆኑን በተለይ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በቁጭት እየገለፁ ይገኛሉ።

የሰሞኑ ገበያም እንደተመለከትነው ከሆነ ከሽንኩርት እስከ ጥራጥሬ..... ከአትክልት እስከ ፍራፍሬ ዋጋቸው ከመጠን በላይ አሻቅቦ ህዝቡ ከሚገዛበት አቅም በላይ እንደሆነበትም ለማረጋገጥ ተችሎዋል።

በተለይ የውጭ ብር ምንዛሪ ከጨመረ ወዲህ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ በሀገር ውስጥ የሚመረቱት ምርቶች ሁሉ ዋጋቸው ከማሻቀቡ በተጨማሪ የምርት እጥረት እንዲፈጠር ወያኔ ሆን ብሎ እየሰራ በመሆኑ ባለፈው ወር ሙሉ ለሙሉ የአትክልት ምርቶች ከገበያ ወጥተው እንደነበረ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በምሬት ገልፀዋል።

ለአምራች ገበሬ ተቆርቋሪ በመመስል ወያኔ ገጠር ድረስ በመግባት ለነጋዴው እንዳይሸጥ ከፍተኛ ቅስቀሳ እና ማስፈራሪያ ሲያደርግ ከርሞ ገበሬው ሙዝ አልሸጥም በማለቱ በስብሶ የተጣለበት ሲሆን ሸማቹም ለአንድ ወር በአይኑ ሳያይ እንደሰነበተ የሚታወስ ነው።

ሙዝ፤ቀይ ሽንኩርት እና ሌሎች አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን ገበሬው ለነጋዴው እንዳይሸጥ ማስጠንቀቂያ በመስጠቱ ከገበያ ላይ ለረዥም ቀናት ከመጥፋታቸውም ሌላ ከትግል ተሰናብተው ወደ ንግዱ ዓለም የገቡት የወያኔ ቀንደኛ ሰዎች በምስጢር በጅምላ እየገዙ በመጋዘን ውስጥ እየደበቁ ህዝቡን በችግር ሲያሰቃዩ እንደሰነበቱም የሚዘነጋ አይደለም።

ሰሞኑን የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ከነጋዴው ማህበረሰብ ጋር በቢሮው መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ማነጋገሩ እና ሲለማመጥ እንደነበር ታውቋል። ሐሙስ ታህሳስ 28 ቀን 2003 ዓ.ም በጠቅላይ

ሚኒስትር ቢሮ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ለአንድ ቀን በተደረገ ውይይት ላይ ነጋዴውን ሲለማመጥ እና ሲያስፈራራ እንደዋለም ተገልፆዋል፡፡

በዕለቱ አሁን ስላለው የገበያ መናር እና መወደድ አስመልክቶ መለስ ዜናዊ ፤በግርማ ብሩ ምትክ የተሾመው አዲሱ የንግድ ሚኒስትሩ እና የጉምሩኩ ባለስልጣን መላኩ ፈንታ ለሶስት ሆነው ማብራሪያና ማስፈራሪያ የሰጡ ቢሆንም ነጋዴዎቹ በድፍረት ምላሽ እየሰጡ እያስደነገጡዋቸው እንደነበረም ከተሰብሳቢዎቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በተለይ መለስ ዜናዊ ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ አስከፊ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚገደድ ሲያስፈራራ የዋለ ቢሆንም ነጋዴዎቹ በበኩላቸው ከእንግዲህ ቢመጣ እስራት እንጂ ሌላ ምን ይመጣብናል በማለት ምላሽ እየሰጡ ሲከራከሩት እንደነበረም ታውቆዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በወያኔ ቁጥጥር ስር ያሉ የንግድ ተቋዋማት ያለ ቀረጥ እና ግብር እንደልባቸው እየተጫወቱ ባለበት ሰዓት ህጋዊ ፍቃድ አውጥተን በአግባቡ እየሰራን ያለነው ላይ ጣት መቀሰሩ የትም አያደርስም ያሉት ነጋዴዎቹ በአንድ ሀገር ሁለት ህግ ወጥቶ የሚሰራበት መሆኑን እያወቃችሁ በእኛ ላይ ብቻ መጮሁ መፍትሔ አያመጣም ሲሉም በንዴት እና በእልህ ሲከራከሩ መዋላቸው ታውቆዋል፡፡

በሀገሪቱ አሉ የተባሉ 500 የሚሆኑ ታዋቂ የንግዱ ሰዎች ጋር ውይይት እየተደረገ ባለበት ሐሙስ ዕለት ከሰዓት በሁዋላ ወያኔ በጎን በኩል እቃዎች ላይ የዋጋ ተመን አውጥቶ በሚዲያ ማወጁ እንዳበሳጫቸው የገለፁት ነጋዴዎቹ የወያኔ ባለስልጣናት ቀድሞም በሸፍጥ ነበር የሚሰሩት አሁንም በዚያው መንገድ ነው የሚጠቀሙት በማለትም የወያኔን መሰሪ ቡድን ሲተቹ ተደምጠዋል፡፡

ከነጋዴው ህብረተሰብ ጋር ውይይት እያደረኩኝ ነው ብሎ በሚዲያ ለማስመሰል ገልፆ ምንም ሳናውቀው እና ሳያነጋግሩን የዋጋ ተመን አውጥተው ይፋ ማድረጋቸው በእጅጉ የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ነው ያሉት ነጋዴዎቹ አሁንም ወደፊትም በህጋዊ መንገድ እየሰራ ያለው የንግዱ ማህበረሰብ ተጎጂ እንጂ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ገልፀው ከበረሀ መጥተው ወደ ንግዱ ስራ የተሰማሩ የወያኔ አባሎች ግን አየር ባየር እየሰሩ ገበያውን እያመሱት እና እያተራመሱት ነው ሲሉም ነጋዴዎቹ በምሬት ገልፀዋል፡፡

ህጋዊ ቁጥጥር እና እርምጃ መወሰዱ ለሀገር እና ለህዝብ ጥቅም መሆኑን የጠቆሙት ነጋዴዎቹ እነ መለስ ግን ለፖለቲካቸው መጠቀሚያ ያደረጉዋቸው ነጋዴዎችን ገበያውን ሲያምሱና ግብር እና ቀረጥ ሳይከፍሉ በነጻ እያፈሱ ያሉትን በአንድ ጀንበር ሚሊየነር የሆኑትን የራሳቸውን ሰዎች መቆጣጠር ትተው ህጋዊ የሆኑት ላይ ማስፈራራት እና አንገት ማስደፋቱ ለወያኔ ውድቀት እንጅ እድገት እንዳልሆነም ሊያውቁት ይገባል ሲሉም በቁጭት ተናግረዋል፡፡

## የወያኔ  እስር ቤት መኮንኖች መሀከል ትርምስ ተፈጠረ፤

## ወያኔ የሀገሪቷን የማእድን ምርቶች እየቸበቸበ ነው ተባለ

## የእቃዎች ዋጋ ግሽበት ተባብሷል፤ በነጋዴዎች ላይ የሚደረገው ወከባም ተጧጡፏል

በሌላ ዜና የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ተብሎ የሚጠራው ወያኔ ዜጎችን የሚያጉርበት መስሪያ ቤት ውስጥ የባለስልጣናት ሹም ሽር መደረጉ ታወቀ::

ሰሞኑን እንደ አዲስ በተጀመረው ሹም ሽረት ነባርና ችሎታ አላቸው የሚባሉ መኮንኖች የተወገዱበት ሲሆን ከበረሀ የመጡት ደግሞ መልሰው ቁልፍ ቁልፍ ቦታችን የተቆጣጠሩበት መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በዚሁ በተደረገው ሹም ሽረት ነባር መኮንኑ ኮሎኔል አለባቸው የተባለው የሸዋ ሮቢት እስር ቤት ዋና አዛዥ ከስልጣኑ ተነስቶ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት ከደረጃው ዝቅ ተደርጎ የሴቶች ክልል ተብሎ የሚጠራው መምሪያ ውስጥ የተመደበ ሲሆን ከበረሀ የመጣው ኮሎኔል የማነ የተባለው የድሬዳዋ እስር ቤት አዛዥ ደግሞ በቅርቡ ስራውን የጀመረው አቃቂ አካባቢ የሚገኘው ቅሊንጦ እስር ቤት ዋና አዛዥ ሆኖ መሾሙን ጥቆማው አስረድቶዋል::

የዝዋይ እስር ቤት ተጠባባቂ አዛዥ የነበረው ከበረሀ የመጣውና የወያኔ ቀንደኛ ባለስልጣኑ ኮሎኔል ገብረየሱስ  መልሶ እዚያው ቦታ ላይ በዋና አዛዥነት የተረከበ ሲሆን የቃሊቲ እስር ቤትን ደግሞ በበላይነት እንዲመራና እንዲቆጣጠር የወያኔው ቁልፍ ሰው ጄኔራል አብርሀም የተባለው መመደቡ ታውቆዋል::

ከሁለት ሳምንት በፊት በተደረገ ሹመት 16 የወያኔ ባለስልጣናት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በሚል በጄኔራል ማዕረግ ሹመት የተሰጣቸው ሲሆን እነዚህ አዲስ ተሹዋሚችም  ሙሉ ለሙሉ የወያኔ ሰች መሆናቸውን እና በየመምሪያው ሁለት ሁለት ሆነው እንዲቆጣጠሩ መመደባቸው ታውቆዋል::

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ብርሀነ መልካ በበረሀ ስሙ ወዲ ሻምበል የሚባለው የወያኔ ባለስልጣኑን ጨምሮ ሌሎች አራት ባለስልጣናት በወርሀ ነሐሴ ድንገት ሳያስቡት እንዲነሱና በእጃቸው ያለውን ንብረት እንዲያስረክቡ ተደርገው የነበረ ቢሆንም ከሶስት ወራት ቆይታ በሁዋላ ተመልሰው ወደ ከፍተኛ ስልጣን መመደባቸው የታወቀ ሲሆን ወዲ ሻምበል የተባለው ግለሰብ የአራት ኪሎ ቤተ መንግስት የመለስን ዙሪያ ጥበቃ የሚያደርጉ ሲቪል ደህንነቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ተደርጎ መሾሙ ታውቆዋል::

ሌሎቹ ሶስት ግለሰቦችም በተለያዩ መስሪያ ቤት ውስጥ በየመምሪያው የተቀመጡ ሲሆን የኮሚሽን መስሪያ ቤቱ የህግ ክፍል ኃላፊ የነበረውና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔር ተወላጁ ኮሎኔል አብዱለጢፍ የተባለው የብሔር ኮታ ማሙያ ተደርጎ ተቀምጦ የነበረው ግለሰብ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር በአንድ መምሪያ ውስጥ የተመደበ ሲሆን  አክሊሉ የተባለው የጄኔራል ማዕረግ ያለው የወያኔ በረሀ አመጣሽ ባለስልጣን የኮሚሽኑ የፋይንናንስ እና ጠቅላላ አገልግሎት ኃላፊ የነበረውም በዚያው በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር የአንድ መምሪያ ሃላፊ ሆኖ መሾሙ ተረጋግጦዋል::

በዝዋይ ፤በድሬዳዋ ፤በቃሊቲ እንዲሁም በሸዋ ሮቢት እስር ቤት ሲሰሩ የነበሩ ቁጥራቸው ከ100 በላይ የሆኑና  በተለይ በወጣት እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ፖሊሶች በድርጊቱ እየተበሳጩ የስራ የመልቀቂያ ጥያቄ ቢያቀርቡም ወደፊት ታይቶ መልስ እስኪሰጣችሁ በስራ ገበታችሁ ላይ እንድትገኙ ይህን ባትፈፅሙ ህገ መንግስቱን እንደ ጣሳችሁ ተቆጥሮ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰድባችሁዋል ሲሉ የኮሚሽኑ ባለስልጣናት ማስፈራሪያ የሰጡዋቸው መሆኑን የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ፖሊሶች በብስጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል:: አንዳንዶቹ የባልስልጣናቱን ትእዛዝ ባለመቀበል ወደ ትውልድ ሀገራቸው የሄዱ መሆናቸው ሲታወቅ በዚህ የተነሳ የጥበቃ ፖሊስ እጥረት በማጋጠሙ አሁን በስራ ላይ ያሉት ፖሊሶች ከሚፈቀደው የጥበቃ ሰዓት በላይ በትርፍ እንዲውሉና እንዲድሩ እየተገደዱ ይገኛሉ::

ባለፈው ዓመት ውስጥ የመጀመሪያ የትራንስፎርሜሽን ለውጥ በሚል በፌዴራል ፖሊስ ውስጥ ብዙ ትርምስ ተደርጎ የነበረና ነባር የወያኔ በረሀ አመጣሽ ባለስልጣናት ወደ ጉምሩክ እና ብሔራዊ ባንክ ውስጥ  ተዛውረው እንዲቆጣጠሩ ተደርጎዋል::

ከእነዚህ ውስጥ የማዕከላዊ እስር ቤት ዋና አዛዥ የነበረው ታደሰ መሰረት እና የፌዴራል ፖሊስ የአድማ በታኝ እና የመረጃ ክፍል ኃላፊ የነበረው ተስፋዬ ፈረሰ የተባሉት ግለሰቦች  የሚገኙበት ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ጉምሩክ ባለስልጣን እና ብሔራዊ ባንክን በስውርም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች ሙሉ ለሙሉ የተቆጣጠሩት የወያኔ አባላት ብቻ መሆናቸው ተረጋግጦዋል::

ኢትዮጵያ በዓመት 290 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር  ከማዕድን ንግድ የምታገኝ ሲሆን ከዚሁም 75 በመቶው ከወርቅ መገኘቱ የሚታውቅ ነው። በአሁኑ ጊዜ በሀገር ደረጃ አጠያያቂና አነጋጋሪ ሆኖ ያለው ጉዳይ ግን ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ሀገር የምትልከው ወርቅ፤ ፕላቲነም፤ ታንታለም፤ መርኩሪ  ወዘተ ሽያጭ

ገንዘብ ብዙ ሚሊዮን ዶላር የት ገባ የሚለው ነው። ብሔራዊ ባንክ ብዙ መቶ ሚሊዮን ብር ከፍሎ ወርቅ ገዛ እየተባለ መሆኑም ጥያቄውን ወቅታዊና ተገቢ ኣድርጎታል። የብሄራዊ ባንክ ተቀማጭ ወርቅ በድንገት በመዳብ ተለውጦ/ሆኖ ተገኘ የተባለውን ያስታውሷል። የወያኔ ወጣት መልዕክተኞች ወደ ሆላንድና ሌሎች ሀገሮች እየተጓዙ የማዕድን ምርቶችን እየሸጡ ገንዘቡን ወደ ወያኔ/መለስ የባዕድ ሀገር ባንክ እንደሚያስገቡ ደግሞ ታውቋል።

ወያኔ የሀገሪቷ ኤኮኖሚ አደገ ተመነደገ እያለ ቢቀላምድም ይህ ሀቅ አለመሆኑን ማመን የተገደደው የማዕከላዊ ስታቲስቲክ ቢሮ የዋጋ ውድነት በ 10. 6 በ መቶ መጨመሩን ማማን ተገዷል። ከምግብ ውጭ ያሉ ዕቃዎች ዋጋ በ 18.7 ጨምረዋል። ሲጋራና ቶባኮ በ 33.9 በመቶ፤ ልብ/ስና ጫማ በ 25.1 በመቶና የህንጻ ቆሳቁሶች፣ነዳጅ ወዘተ ደግሞ በ 16.5 በ መቶ ዋጋ መጨመራቸው ተረጋግጧል።የብር ዋጋ ወይም የምንዛሪ አቅም በመቀነሱ የተነሳ የኑሮ ውድነት ዋጋው ወይም የዕቃዎች ውድነትና ዋጋ ወደፊት ይበልጥ መጨመሩ አይቀርም ተብሏል። የሕዝብ የኤኮኖሚ አቅም እየደቀቀ እን.ጂ እየተጠናከረ አይሄድም ማለት ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ የአዲስ አበባ አስተዳደር በኢንዱስትሪ አልሚዎች ላይ ዘመቻ ጀመረ የሚለው ዘገባ በስፋት ተደምጧል። በአዲስ ኣበባና አካባቢዎቿ በልማት እንሰማራለን ብለው ብለው መሬት ተመርተውና ከልለው የረባ እንቅስቃሴ አላደረጉም ያላቸውን ንብረት የኩማ ደመቅሳ አስተዳደር ቀምቶ ወስዷል። ይህ እርምጃ ደግሞ ለወያኔ ጎንበስ ደፋ ማለት የጀመረውን አትሌት ሀይሌ ገብረስላሴንም ማጥቃቱ ተዘግቧል። አትሌቱ በአፍቅሮ ወያኔ ተያዝኩ ብሎ ሕዝብን መስደቡና ማስቀየሙ የሚታወቅ ሲሆን ወያኔ ስልኬን ጠለፈ፤ የፖለቲካ ተጽዕን አደረገብኝ ያለውን ግን መልሶ መካድ ተገዷል። ሀይሌ ገብረስላሴ ወደ ሩጫ ተመለስኩ ቢልም ያለፈውን ዝናውን ሆነ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነቱን ግን ማጣቱን ታዛቢዎች ያረጋግጣሉ። የሕዝብን ቤት ንብረት ለመቀማትና ለወያኔ ቱጃሮች ለመስጠት በአርከበ ዕንቋይ ተጀምሮ የነበረው ዕቅድ በስፋት በኩማ ደመቅሳ ሊቀጥል መዘጋጅቱም ታውቋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሰሞኑን በነጋዴዎች ላይ የሚደረገው አፈና ተጧጡፎ የቀጠለ መሆኑ ታውቋል። ወያኔ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ ከአጋሮቹ ጋር ሆኖ በቁጥጥር ለማስገባት በሚያደርገው ያላሰለሰ ጥረት በአዲስ አበባ ከተማ በገንዝብ ምንዛሪ የተሰማሩትን ዜጎች ለማፈን ከዚህ ቀድም ድንገተኛ አሰሳ ማካሄዱና በብዙ ሚሊዮን ብር የሚቆጥር ገንዘብ መውረሱ የሚታወስ ነው። በሰሞኑ ደግሞ 47 ነጋደዎችን አፍሶ በሃዋላ ወይም ወያኔ ህገውጥ በሚለው የገንዘብ ምንዛሪ እንቅስቃሴ ተሰማርተዋል በሚል ክስ ኣስሮ ለፍርድ ሊያቀርብ ተዘጋጅቷል። ዋናው ዓላማ ግን በሀገርም ውስጥ ሆነ በውጭ ሀገር ወያኔ የገንዘብ ምንዛሪ እንቅስቃሴውን

ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር መሆኑ ግልጽ ነው። በዚህም መስከ የተዟዟፈ ስምሪት ይዛ ያለችው ያው የለመደባት የመለስ ሚስት አዜብ መሆኗም የሚታወቅ ነው።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ባወጣው መግለጫ በየመን ሀገር የሚኖሩ ሺዎች ስደተኞች አስቃቂ በደል እየደረሰባቸው መሆኑን አጋልጦ የተባረኡት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን ተልዕኮውን እየተወታ አለመሆኑንም ወቅሷል። የዚሁ ኮሚሽን ባልስልጣኖችም ስደተኞችን ብሄርሰባችሁ ማነው ብለው ከመጠየቃቸው ሌላ ኢትዮጵያዊ ናችሁ ኦሮሞ የሚሉት ጥያቄ አግባብን ያጣ መሆኑም ተወግዟል። ባዕዳን ዜጎችን በብሄረሰብ ደረጃ ለመከፋፈል ይሁነኝ ብለው መጣራቸውን የስደተኛው ኮሚሽን ድርጊት ያጋልጣል ተብሏል። ተቀማጭነቱ ጀርመን ዋና ከተማ የሆነው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በሌላ በኩል የበርማዋ የሰላም ታጋይ ኣንግ ሱን ቺ መፈታትዋን ደግፎ ግን የሷን መፈታት ግሩም ያሉና ቀሪዎቹም የበርማ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ያሉት ምዕራባውያን በኢትዮጵያ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ ሲሉ ኣልተደመጡም ሲል አማሯል።

ወያኔ ከሶማሊያ የተገነጠለችውን ሶማሊላንድን በ ዓለም ዓቀፍ ደረጅ እውቅና ለማሰጠት ደፋ ቀና እያለ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ከአሜሪካና እንግሊዝ ጋር በማበር ደቡብ ሱዳንን ለማስገንጠል ጥረቱን አጧጡፏል። በአሁኑ ውቅት ስድተኞችን ጨምሮ ከ 2000 ኢትዮጵያውያን በላይ በድቡብ ሱዳን ዋና ከተማ ጁባ የሚገኙ ሲሆን በርካታ የወያኔ ስላዮችም በዚሁ ከተማ መሠማራታቸው ግልጽ ሆኗል። በጁባ አክሱም ቡናና አዝማሪ ቤት የሚታዩት ስላዮችም ድቡብ ሱዳን ትገነጠላላች ብለው ኣፋቸውን ሞልተው እየደነፉ መሆናቸውም ተደምጧል።የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ጁባ በሳምንት ኣራት ጊዜ ሲበር ከርሞ በተጨማሪ ወደ ማላካል ከተማም መብረር መጀመሩ ሲነገር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ጁባ ከተማ ቢሮ ከፍቷል። በርካታ የሻዕቢያ ሰራትኞችም ጁባ ከተማ መገኘታቸው የሚታይ ነው። ፉክክሩ የተዟዟፈ ስሆን ሳለ አመሪካም የመለስን አገዛዝ በመጠቀም ሰላዮቹን ማሰማራቱ ሊደበቅ ያልቻለ ህቅ ነው። ድቡብ ሱዳንን ለማስገንጠል ሕዝበ ውሳኔው በመጪው ጥር መካሄዱ ራሱ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ደቡብ ሱዳን መገንጠልን መምረጡ አይቀሬ ነውና ይህን ውጤት የሱዳኑ መሪ በሺር በቀና ከተቀበለ የስልጣን ዕድሜው ማጠሩ አይቀርም የሚሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች ብ/ዙ ናቸው። በሱዳን አዲስ ጦርነት ምከፈቱም የሚጠበቅ ነው። ይህ በዚህ እንዳለ ባለፈው ሰሞን በካርቱም የወያኔ ስላዮችና አፋኞች ሀለፎም ወይም ክብሮም የሚባል የቀድሞ የወያኔ የደህንነት አባል ጠልፈው ወደ ኢትዮጵያ መውሰዳቸው ታውቋል። ግለሰቡ በ1987 ዓ.ም. በወያኔ፤ሻዕቢያና የደቡብ ሱዳን ነጻ አውጪ ግንባር መሪዎች መሀል በአዲስ አበባ ተካሂዶ በነበረው ስብሰባ የወያኔ ተወካይ ሆኖ የተሳተፈ እንደነበርም ለማውቅ ተችሏል። በዚሁ ስብሰባ ወያኔ

ጋምቤላን ነጻ ለምትሆን ደቡብ ሱዳን ኣሳልፎ ለመስጠት ተስማምቶ ነበር መባሉም የሚዘነጋ አይደለም። ሀለፎም መጠለፉ ብዙ ምስጢርን እንዳያወጣ እነ መለስ ስጋት በመግባታቸው ነውም ተብሏል።